# እውን ገድል ሆነ?

**ከዓሣዩ**

03/30/2010

**ኣዎ ገድል ሆነ! ቀንዲል ተለኮሰ!**
የጠላትን ዝርዝር እያተራመሰ
ከዚቁ ሊከተው እያፈራረሰ፣
በታጠፈው ኣገር በተሸበለለ
ባላባቱ እያለሁ ማን ቆርጦት እያለ
የነ ኣጅሬው መንደር ባባቱ እየማለ ።
ዝናሩን ዘንሮ
ቀይ እርሣሥ ቀርቅሮ፣
ቤንዚኑን ነሥንሶ
ክብሪቱን ለኩሶ፣
ሰደድ ለቀቀበት ኣንበሣው ፎክሮ
የወያኔን መንደር  ዙሪያውን መትሮ ።
**ኣዎ ገድል ሆነ!**
ከእንግዲህ ማምረሩን ለይቶት እንዲያውቀው
የዘረኛን ክምር ፣ የደለበን ሙክት ፣ በእሣቱ እያጋየው ።
ግዜውን ጠብቆ የጧት ጎሕ ፈንጥቆ
የደፋቂው ከንፈር እንደ ኩበት ደርቆ
ሌባ ጣቱ ፈዞ ዓይኑ ብቻ ፈጦ
ብርክ ኣንቀጥቅጦታል፣ኣይደርሥ ያለው መጥቶ ።
**ጉዱ ኣሁን ሊታይ ነው!**
ወንበር ምታንኳኩ ለወንበር ሰግዳችሁ
በሥነ ምግባር ልጓም እጅ ተወርች ታሥራችሁ
የሕዝቡን ጥያቄ ወደ ጎን ትታችሁ
የታሪክ ቀልባሹን በምርጫ ኣጅባችሁ
እንዳሣደገው ልጅ እንዳሻው ሲያዛችሁ
**ትዕዛዙን በመጣሥ እምቢኝ! ካላላችሁ**
እሥቲ ምከሩበት ሕዝብ እንዳይጠላችሁ
**በታሪክ ተወቃሽ እንዳያደርጋችሁ! ።**
ቀንዲሉ  በርቷል የለም ሌሊት
ገድሉ ጀምሯል ኣልፎ ክረምት
ጀግኖች ከፈሪ ሊለዩበት
ሃገር እንዳትፈርሥ ሊታደጓት! ።
**ኣዎ ገድል ሆነ! ቀንዲል ተለኮሰ!**

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.